አፍሪካ ቲቪ

1

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት

በቴሌግራም

6

አፍሪካ አካዳሚ
AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

## “ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት”

## የሴት ልጅ የተፈጥሮ ደም

እንደሚታወቀውም ሴቶች በተለያዩ ምክንያቶች የተለያዩ የደም ዓይነቶች ይፈሷቸዋል።
ከነዚህም መሀከል

- የሀይድ (የወር አበባ) ደም
- የኢስቲሃዳ (የበሽታ) ደም
- የኒፋስ (የወሊድ) ደም…



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- **1. ሐይድ (የወር አበባ)፦**
- የቋንቋ ትርጉሙ፡-መፍሰሥ ማለት ሲሆን
- በሸሪዓዊ ትርጉም ደግሞ የሀይድ ደም ማለት በተፈጥሮ እና ከጤናማነት ማህፀን የሚያመነጨውና ሴቷ ለአቅመ ሀዋእ ስትደርስ በተወሰነ ጊዜ የሚመጣ እና በተወሰነ ጊዜ የሚሄድ አብዛኛውን ጊዜ በየወሩ የሚፈስሳት የደም አይነት ነው።

1

አፍሪካ አካዳሚ

# በመጀመሪያ፡ የወር አበባ እና የበሽታ ደም

| ጉዳዩ | ብይኑ |
|---|---|
| ሴት ልጅ የወር አበባ ማየት የምትጀምርበት ትንሹና ልታቆምበት የምችለዉ ከፍተኛ እድሜ | አነስተኛው ዘጠኝ አመት ሲሆን፤ ከዚህ በፊት የምታየው ደም ሁሉ የበሽታ ደም ነው፡፡ ደም የምታቆምበት ግን ገደብ የለውም |
| አነስተኛ የወር አበባ የሚቆይበት ቀናት | ሀያ አራት ሰዓት ነው፡፡ |
| ከፍተኛ የወር አበባ የሚቆይበት ቀናት | አስራ አምስት ቀናት ነው፡፡ ከዚህ ቁጥር በላይ ካየች የበሽታ ደም (ኢስቲሃዷ) ነው፡፡ |

1

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ
ኢስላማዊ ቤተሰብ ህግጋት

አፍሪካ አካዳሚ

## የወር አበባ (ሀይድ) ወይም የወሊድ ደም ላይ ያለች ሴት ከምን ትከለከላለች?

- **1ኛ፡**- የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም ያየች ሴት የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም ክልክል (ሐራም) ነው፡፡

አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ እንዲህ ብሏል፡-

(وَيَسْأَلُونَكَ عَنِ الْمَحِيضِ قُلْ هُوَ أَذىً فَاعْتَزِلُوا النِّسَاءَ فِي الْمَحِيضِ وَلا تَقْرَبُوهُنَّ حَتَّى يَطْهُرْنَ) [البقرة ٢٢٢]

(ስለ የወር አበባም ይጠይቁሃል፡፡ እርሱ አስጠያፊ ነው፡፡ ሴቶችንም በወር አበባ ጊዜ ራቋቸው፡፡ ንጹሕ እስከሚኾኑም ድረስ አትቅረቡዋቸው፡፡)

- በማለት ባዘዘን መሰረት ማንኛውም ባል በዚህ ወቅት ከሚስቱ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀሙ ሀራም በመሆኑ ይከለከላል። ሚስትም ለሱ እንዳትመቻች ትከለከላለች።

1

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

- ከዓኢሻ ረዲየላሁ ዐንሃ በቡኻሪና ሙስሊም ዘንድ በተዘገበው መሰረት
  كان النبي صلى الله عليه وسلم ، يأمرني فأتزر فيباشرني وأنا حائض . متفق عليه .
  (ነቢዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ሀይድ ላይ ስሆን ሽርጥ እንድለብስ ያዝዙኝ ነበርና ሽርጥ ከለበስኩ በኋላ ያቅፉኝ ነበር።» ብላለች።
- በዚህ መሰረት በሀይዳቸው ወቅት የሩካቤ ስጋ ከመፈፀም መጠንቀቅ ይኖርብናል። ስሜቱን መቆጣጠር ለማይችል ሰውም መተሻሸትን የመሳሰሉት ተግባራት ወደ መጨረሻው እንዳያዘልቀው ከሰጋ ሊጠነቀቀውና ሊርቀው ይገባል።

1

አፍሪካ አካዳሚ

- 2) የወር አበባ ፍቺን ያግዳል
  አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላ እንዲህ ይላል፡-
  ( فَطَلِّقُوهُنَّ لِعِدَّتِهِنَّ)
  (ሴቶችን መፍታት ባሰባችሁ ጊዜ፤ ለዒዳቸው ፍቱዋቸው፡፡) ብሎ ስላዘዘን ባል ከሚስቱ ጋር ለፍቺ የሚያበቃቸው ጉዳይ ቢገጥመው እንኳ ፍቺ በሚፈቀድበት ወቅት እንጂ በየወር አበባዋ ላይ ባለችበት ወቅት ሊፈታት እንደማይገባው አስጠንቅቋል።

1

አፍሪካ አካዳሚ

- ከዚህ ውጭ ሀይድ ላይ እያለች ባል ሚስቱን ቢፈታ ወንጀለኛ ነው። ተውበት ሊያደርግም ይገባዋል። ሚስቱንም በጥላው ስር መልሷት ከአላህና ከመልእክተኛው መመርያ ጋር በሚስማማ መልኩ ሸሪዓዊ ፍቺ ሊፈታት ይገባል።
- በዚህም መሰረት ፊቺውም ስለሚወድቅ ከመለሳት በኋላ ከዚያ ከፈታበት ሀይዷ እስከትነፃ መጠበቅ አለበት። ከዚህም በኋላ እንደገና ሀይድ ማየት አለባት። ከዚህ በኋላ ከሀይዷ ስትነፃ ከፈለገ በትዳሩ ይቀጥላል። ካልሆነ ግን ሩካቤ ስጋ ሳይፈፅምባት ይፈታታል።

1

አፍሪካ አካዳሚ

- 3) ሰላት መከልከል
- የወር አበባ ላይ ላለች እንስት የፍላጎትንም ይሁን የግዴታ ሰላትን መስገዷ ይከለከላል።
- ከሀይድ በነፃቸበት ወቅት የሰላቱ ወቅት አንድ ረከዓ የሚያሰግድ ያህል ካልቀራት በስተቀርም እንድትሰግድ አትገደድም።
- ይህም የሰላቱ ጅምር ወቅት ላይ ይሁን የመጨረሻው ወቅትም ላይ ቢሆን የደረሰችው ሙሉ አንድ ረከዓ የሚያሰግዳት ግዜ እያለ እሷ ንፁህ ከሆነች
  ቶሎ መስገድ አለባት።

1

- 4) የወር አበባሽ ከመፆም ያቅብሻል
- የወር አበባ ላይ ላለች እንስት የፍላጎትም ይሁን የግዴታ ፆምን መፆም ይከለከላል። ብትፆምም ትክክለኛ አይደለም።
- በወር አበባዋ ወቅት ያለፋትንም እለታት ነፃ በሆነች ግዜ በመፆም ማካካስ ግድ ይሆንባታል።

አፍሪካ አካዳሚ

- 5) የወር አበባ በካዕባ ዙርያ ከመጠወፍና መስጂድ ውስጥ ከመቀመጥም ያግድሻል

ነቢዩ ሰለላሁ አለይሂ ወሰለም ባለቤታቸው ዓኢሻ ረዲየላሁ ዐንሃ ለሐጅ ከተጓዘች በኋላ የወር አበባዋ ስለመጣባት
(افعلي ما يفعل الحاج غير ألا تطوفي بالبيت حتى تطهري)
(እስክትነፂ ድረስ በአላህ ቤት (በካዕባ ዙርያ) ጠዋፍ አታድርጊ እንጂ ሌላውን ሀጅ አድራጊ የሚያደርገውን ሁሉ ተግብሪ።» ባሉት መሰረት ማንኛዋም
ሀይድ ላይ ያለች እንስት የፍላጎትም ሆነ የግዴታ የሆነን
ጠዋፍ ማድረጓ ትክክል አይደለምና መቆጠብ አለባት።

1

አፍሪካ አካዳሚ

- **6) ዚክር እና ቁርኣንን መቅራት**
- የወር አበባ ላይ ያለች እንስት አላህ ሱብሃነሁ ወተዓላን የምታወሳበትን ቃላቶች እንደ ተስቢህ፣ ታህሚድ፣ ተክቢርና ስትመገብ ቢስሚላህ ማለትን የመሳሰሉ እንዲሁም ሃዲስን ማንበብ፣ የፊቅህ ኪታቦችን ማንበብ፣ ዱዓእ ማድረግ፣ ዱዓእ ሲደረግ ኣሚን ማለት እና ቁርኣንን ማድመጥ በሙሉ ያለ ምንም ተቃውሞ ይፈቀድላታል። ነገር ግን
- የኢስላም ሊቃውንት እንዳስረዱት አስፈላጊ ጉዳይ ካልገጠማት በስተቀር ሀይድ ላይ ያለች እንስት ቁርኣንን በአንደበቷ ባታነብ የተሻለ ነው።።
- ለምሳሌ:
- ⁜~ የቁርኣን አስተማሪ ከሆነችና ተማሪዎቿን ማረም ካስፈለጋት ብታነብ ወቀሳ የለባትም።
- ⁜~ እንዲሁም የቁርኣን ተማሪ ከሆነችና ሀይዷ የመጣባትም በዚሁ በፈተና ወቅቷ ከሆነ ለፈተናው ስትልና ለመሳሰሉት አስፈላጊ ጉዳዮች ብታነብ አግባቢ እንደሆነ ሊቃውንት ያስረዳሉ ።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com